# የማጠናከሪያ ክትባት ከ mRNA ክትባት ጋር (Pfizer/BioNTech, Moderna)

**የmRNA ክትባቶች በሆስፒታል ውስጥ ተኝቶ መታከምን ከሚያስከትል ከባድ በሽታን በሚገባ ይከላከላሉ። ይሁን እንጂ፣ ይህ የመሰረታዊ ክትባቶች መከላከያ አሁን ባሉት የቫይረስ ዝርያዎች በፍጥነት ይቀንሳል። ዕድሜው 12 ዓመት የሞላው ማንኛውም ሰው የማጠናከሪያ ክትባቱን እንዲወስድ እንመክራለን።**

## የማጠናከሪያ ክትባቱ ዓላማ ምንድን ነው?

የማጠናከሪያ ክትባቱ የበሽታ መከላከያ ስርዓት ፓቶጂንን እንዲያስታውስ ያደርገዋል። የማጠናከሪያ ክትባቱ ለበሽታ መከላከያ ስርዓታችን ስለ ፓቶጂን ያስታውሰዋል። ክትባት ከከባድ በሽታዎች የሚሰጠን መከላከያ በድጋሚ የሚጨምርና የሚራዘም ይሆናል።

ይህን ማወቅ ይገባ፡- አሁን ባለው ተለዋዋጭ የቫይረስ ዝርያ ምክንያት ክትባቱ በቂ መከላከያ የማይሰጥ ሲሆን፣ ቢከላከልም ኢንፌክሽን እና መጠነኛ በሽታን ብቻ ነው። ክትባቱን ቢወስዱም እንኳን በኮቪድ-19 ሊያዙ ይችላሉ።

## የማጠናከሪያ ክትባት እንዲወስዱ የሚመከሩት እነማን ናቸው?

<u>ዕድሜያቸው 12 ዓመትና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች የማጠናከሪያ ክትባት ይመከራል።</u>

- ምክረ ሃሳቡ ተፈጻሚ የሚሆነው በተለይ ለኮሮና ቫይረስ ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ነው፡-
- ዕድሜያቸው 65 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች
- ስር የሰደዱ በሽታዎች ያሉባቸው ዕድሜያቸው 16 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች[1]
- ነፍሰ ጡር ሴቶች

## የማጠናከሪያ ክትባት መጠሰት ያለበት መቼ ነው?

መደበኛ የ mRNA ክትባት ሙሉ በሙሉ ከተወሰደ ከ4 ወራት በኋላ ክትባት መውሰድ ይመከራል። የተሟላ መሰረታዊ በሽታ የመከላከል አቅም የሚፈጠረው

- የ mRNA ክትባት በሁለት ዙር ከተሰጠ በኋላ፤ ወይም
- በኮሮና ቫይረስ ኢንፌክሽን መያዙ ከተረጋገጠ እና ቢያስን ከ4 ሳምንት በኋላ አንድ የ mRNA ክትባት ከተሰጠ (ቅደም ተከተሉ ምንም ቢሆን)።

መሰረታዊ ክትባቱን ከወሰዱ በኋላ በኮሮና ቫይረስ ቢያዙም እንኳን፣ የማጠናከሪያ ክትባቱን እንዲከተቡ እንመክራለን። በአዳዲስ ግኝቶች መሰረት፣ ኢንፌክሽን ከከባድ በሕታ በቂ መከላከያ አይሰጥም። በበሽታው ከተያዙ ከአራት ሳምንታት በኋላ መከተብ ይችላሉ (የመጨረሻውን የኮቪድ-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ መጠበቅ ያለበት ቢያንስ 4 ሳምንትን ከግምት ውስጥ በማስገባት)።ለማጠናከሪያነት የሚውለው ክትባት የትኛው ነው?በመርህ ደረጃ፣ አሁን ካሉት ሁለት የ mRNA ክትባቶች ጥቅም ላይ የዋለው የትኛው ነው የሚለው አሳሳቢ አይደለም።

ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች ለሆናቸው ሰዎች፣ የሚከተለው ተፈጻሚ ይሆናል፡- ዕድሜያቸው ከ18 እስከ 29 ዓመት የሆናቸው ግለሰቦች የ Pfizer/BioNTech ክትባትን በማጠናከሪያነት እንዲከተቡ ይመከራል። ዕድሜያቸው ከ12 እስከ 17 ዓመት የሆናቸው ግለሰቦች የ Pfizer/BioNTech ክትባትን በማጠናከሪያነት እንዲከተቡ ይመከራል። የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ክትባቱ እንደተወሰደ ወዲያውኑ የልብ ጡንቻ ማበጥ ሁኔታ በጣም አልፎ አልፎ ስለተከሰተ ነው። እንዲህ ዓይነት የጤና ችግር ተደጋግሞ የታየው Pfizer/BioNTech ክትባት ሳይሆን የ Moderna ክትባት ከተወሰደ በኋላ ነው። ይሄ በጣም አልፎ አልፎ የሚከሰት የጎንዮሽ ጉዳት ሲሆን ተገቢው ሕክምናም አለው። በኮሮና ቫይረስ ከተጠቁ በኋላም እንዲህ ዓይነት እብጠት ይከሰታል። ይሁን እንጂ፣ በሁለቱም የ mRNA ክትባቶች፣ ዕድሜያቸው ከ30 ዓመት በታች በሆኑ ሰዎች ላይም እንኳን የኮቪድ-19 ክትባት ጥቅም ከስጋቶች የበለጠ ነው።

## ክትባቱን መውሰድ የምችለው የት ነው?

ክትባቱን የመስጠት ሃላፊነት የወረዳዎች ነው። የት ተመዝገበው መከተብ እንደሚችሉ ለማወቅ የወረዳዎን ድረ ገጽ ወይም የመረጃ መስመር ይመልከቱ (www.foph-coronavirus.ch/cantons)።ወይምዶክተርዎን፣ ፋርማሲስትዎን ወይም ፋርማሲዎን ያነጋግሩ።

## የማጠናከሪያ ክትባት የሚመከረው ለማን ነው (የመጀመሪያው የማጠናከሪያ ክትባት ከተሰጠ በኋላ)?

በአሁኑ ጊዜ፣ ዕድሜያቸው ከ80 ዓመት በላይ ለሆናቸው ሁሉም ሰዎች ተጨማሪ የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ ይመከራል። በሽታ የመከላከል አቅማቸው እጅግ ለተዳከመ ሰዎች (በበሕታ ወይም በመድሐኒት ምክንያት) ተጨማሪ የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድን እንመክራለን - እንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲከሰት፣ እባከዎ ዶክተርዎን ያማክሩ።

የመጨረሻው ክትባት ከተወሰደ ከ4 ወራት በኋላ ሌላ የማጠናከሪያ ክትባት መውሰድ ይቻላል። ቢያንስ ለተወሰነ ጊዜ በከባድ በሽታ እንዳንጠቃ የክትባት መከላከያን ይጨምራል።

የመጨራሻውን ክትባት ከተከተቡ በኋላ በኮሮና ቫይረስ ተይዘው ያውቃሉ? ይህ ኢንፌክሽን ከከባድ በሽታ የመከላከል አቅምዎትን በከፍተኛ ሁኔታ ያልጨመረው በመሆኑ፣ ሌላ የማጠናከሪያ ክትባት እንዲከተቡ እንመክራለን። በበሽታው ከተያዙ ከአራት ሳምንታት በኋላ መከተብ ይችላሉ (የመጨረሻውን የኮቪድ-19 ክትባት ከወሰዱ በኋላ መጠበቅ ያለበት ቢያንስ 4 ሳምንትን ከግምት ውስጥ በማስገባት)።

**የቀረው መረጃ ለማጠናከሪያ ክትባትና ለመደበኛ ክትባት ተመሳሳይ ሲሆን፣ በዚህ የመረጃ ቅጽ ላይ ይገኛል፡ «*የኮቪድ-19 ክትባት የሆኑትን mRNA ክትባት የተመለከተ አጠቃላይ መረጃ*».**

[1] *ዝርዝር የበሽታዎች ዝርዝር በልዩ ሁኔታ ለአደጋ የተጋለጡ ሰዎች ምድቦች (PDF, 205 kB) ማግኘት ይቻላል*